ግንቦት 6ቀን 2013ዓ.ም.

**ክቡር ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ከዚህ ዓለም የተለዩበትን 22ኛ ዓመት አሥመልክቶ የወጣ መግለጫ!**

ሰማዕቱ ክቡር ፕሮፌሰር አሥራት ወልደዬስ የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት(የመዐሕድ)ፕሬዝዳንት የዛሬ 22ዓመት ግንቦት 6ቀን 1991ዓም(እ አ አ ሜይ 14ቀን 1999ዓም) በፔንሲልቫንያ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ፊላደልፊያ አሜሪካ አገር በህክምና ላይ ቆይተው ከዚህ ዓለም እንደተለዩ ይታወቃል።

ክቡርነታቸው! የአማራን ሕዝብ የህልውና እና የመኖር ዋስትና ተግባራዊ ለማድረግ ከመጣራቸውም ሌላ ለኢትዮጵያ ሀገራዊና ሕዝባዊ አንድነት እንዲሁም እኩልነትና ዲሞክራሲያዊ ሕይወት ግኝት የከፈሉት አቻ የለሽ መሥዋዕትነት፣በታሪክ ዓምድ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ከመያዙም ባሻገር፣ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የሚኖር ነው።

ፕሮፌሰር! በ1983ዓም የትግሬና የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባሮች(የትነግና የኦነግ) ዕድምተኞች አማራን በማግለል ያካሄዱትን የኢትዮጵያን ሀገራዊና ሕዝባዊ አንድነት የመናድ ተግባር፣የኮንፈረንሱን ምንነትና ተልዕኮ፣ የመጣውም የጎሳ ፖለቲካ ገና ከመነሻው ችግር ሊያሥከትል እንደሚችል በግልፅ ከመናገር አንሥቶ በአማራው ላይ የመከራ እሳቱም ሲቀጣጠል ያንን ለማጥፋት በቀዳሚነት የተሰለፉ እና ድምፃቸውን አጉልተው ያሠሙ ብቸኛው የቁርጥ ቀን ልጅ ነበሩ።

እንደሚታወቀው በ1983ዓ.ም.የደርግ መንግሥት ወድቆ ኢሕአዴግ ሲተካ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ፋካልቲ ዲን ነበሩ።የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን በመረጧቸው መሠረት በሰኔ 1983ቱ ኮንፈረንስ ላይ ተገኝተዋል።በኮንፈረንሱ ላይኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል የሚፈቅደውንና"መገንጠል" የኢትዮጵያ የወደፊት መተዳደሪያ እንዲሆን የሚያረጋግጡትን አንቀጾች የተቃወሙ ብቸኛ የጉባዔ ተሳታፊ ነበሩ።
በተለይ ስለኢትዮጵያና ስለኤርትራ ታሪክ የተሰጠውን ትንተና የማይቀበሉት መሆኑን ሲገልፁ፣
"ይህ ጉባዔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ምንም ጉዳይ ሊወስን ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ አይችልም። ሆኖም የኢትዮጵያን የአሁኑን ተጨባጭ ሁኔታ በመመርኮዝ የወንድማማቾች ደም መፋሰስ የቆመ በመሆኑ አሁን የሰፈነ የሚመስለውን የሰላምና የዲሞክራሲያዊ ሂደት መሠረት በማድረግ፡ የኢሕአዴግና የሕዝባዊ ግንባር ሀርነት ኤርትራን ልዩ ግንኙነት በመጠቀም ወንድማማችና እህትማማች በሆነው ህዝብ መካከል የዘለቄታ ቅራኔ እንዲወገድና በኢትዮጵያዊነትና በይቅር ለእግዚአብሔር ባይነት መሠረት በአስቸኳይ የሚስማሙበትን መንገድ መፈለግ ለመሸጋገሪያ መንግሥት ተቀዳሚ ተግባር እንዲሆን ጉባዔው እንዲያሳስብ ይህን ሀሳብ በአክብሮት አቀርባለሁ " ነበር ያሉት።

ከዚህ ኮንፈረንስ በኋላም የዩኒቨርሲቲ ምሁራንን በመወከል በተቋቋመው የሽግግር መንግስት በተወካዮች ምክር ቤት አባልነት እንዲሰሩ ተደጋጋሚ ጥሪ ተደርጎላቸው አልተቀበሉትም።የኤርትራን መገንጠል በግልጽ መቃወማቸውና ተቋቋመ በተባለው የተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ላለመሳተፍ የወሰዱት ቁርጠኛ አቋም በሻዕቢያ፣በትነግ፣በኦነግ እና በሌሎቹም ገንጣዮችና አሥገንጣዮች ጥርስ ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል።

ፕሮፌሰር!ዐማራው ዐማራ ሆኖ በመፈጠሩ ብቻ፣ከሌሎቹ በተለዬ የግፍ ፅዋ ቀማሽ እና አለሁ ባይ ተቆርቋሪ የሌለው መሆኑን በመገንዘባቸው፣ከጨርሶ መጥፋት ለማዳን እና አገር የማፍረስ፣ ኢትዮጵያውያንን በዘር በጎሳና በጎጥ እየለዩ እርስ በርስ የማጫረስ አፍራሽ ፖሊሲን የዘረጋውን ሥርዓት ለመታገል ቆርጠው ከተነሱ ወገኖቻቸው ጋር በመምክር በሰላማዊ መንገድ የመደራጀትን አስፈላጊነት አመነውበት መዐሕድን አቋቋሙ።በፕሬዚዳንትነትም መሩት።

ዐማራው! በሐረር፣በአርባጉጉ፣በበደኖ፣በአረካ፣በአሰቦት ገዳም፣በአሩሲና በተለያዩ የአገሪቱ ክፍል መታሰሩ መሰደዱ፣ህይወቱ እያለ ዓይኑ ሲጎለጎል፣ሕይወቱ እያለ ቆዳው ሲገፈፍ፣ሕይወቱ እያለ ሥጋውን ቆርጠው “ብላው እያሉ” ሲያሰቃዩት፣ሕይወቱ እያለ ቤት ዘግተው ሲያቃጥሉት፣ሕይወቱ እያለ ወደገደል ሲወረውሩት፣ሕፃናት ከእነቤተሰቦቻቸው ሲታረዱ፣የዕርጉዞች ሆድ ሲቀደድና ሽሉ ሲጣል፣ የዐማራው ልጃገረዶች ሲደፈሩ፣ሲዋረዱና ተማርከው በባርነት ሲያገለግሉ፣አብያተ ክርስቲያናት ሲቃጠሉና ሌሎችም ተዘርዝረው የማያልቁ የዘር ማጥፋት ሰቆቃዎች ሲፈፀሙበት፣ፕሮፌሰር አሥራት! ዙሪያ ገባውን በጠላት ቢከበቡም፣ ችግርና ፈተና ሳይበግራቸው፣ከፊት ለፊታቸው የተጋረጠውን ግዙፍ ኃይልና አደጋ ከምንም ሳይቆጥሩ፣በቁርጠኝነት በመቆም በዚህ በቀውጢ ሰዓት ከማንም ቀድመው ይህንን እኩይ ሥርዐት ያለመታከት በማጋለጥ የአማራው ሕዝብ የሚፈፀምበትን ወንጀል እንዲረዳና እንዲታገል፣ዓለምም እንዲያውቀው በማድረግ፣በታላቅ ቆራጥነት ታግለው ”ዴሞክራሲያዊ ነኝ ”ባዩን ትነግን እርቃኑን ማስቀረታቸው አርአያነቱ ምንጊዜም የማይረሳ ነው።

ፕሮፌሰርም በአንድ ወቅት <u>“በአራት እግሩ በመሄድ ላይ የነበረው ዐማራ አንገቱን ቀና አድርጎ በሁለት እግሩ መሄድ ጀመረ</u>” ማለታቸውን እናስታውሳለን።ይህም የመጀመሪያው የፕሮፌሰር አሥራት ቆራጥ አመራር የሕይወት ፍሬ ውጤት ነበር።

በዚህን ጊዜ የመዐሕድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍ ያለ ሕዝባዊ ተቀባይነትን የማግኘት እርምጃ፣ትነግ! በኦነግ ተባባሪነት ”አማራን ለማጥፋት” የገነባው <u>”ሥርዓት፣ህገመንግሥትና የዘር ፌደራሊዝም”</u> የሚፈርሥበት መሥሎ ሥለታዬውና ሥላሥደነገጠው፣

(1)”ነፍጠኞች፣ ትምክህተኞች፣ያለፈው ሥርዓት ናፋቂዎች ” ወዘተ ...እያለ እግር በእግር እየተከታተለ በመገናኛ ብዙሀን ጭምር ከማውገዝም አልፎ፣አባላትና መሪዎችን መግደል ማቁሰል ማፈን ማሰርና ማስፈራራቱን በገሀድ አደረገው።

(2)ትነግ! መዐሕድን ከእነመሪው ለማጥፋት የተጠቀመበት ሌላው አደገኛ መንገድ፣እንደዛሬው ”ኢዜማ” በኢትዮጵያ ሥም የሚመፃደቀውን ”ኢሕዴን” የሚባለውን አማራ ጠል ድርጅት በአንድ ቀን ጀምበር የአማራ ሥም ሠጥቶ ወደ ”ብአዴን” ቀይሮ ለአማራ የቆመ መሥሎ አማራውን ከፋፍሎ እንዲያዳክም እና ከመዐሕድ አመራርና አባላት መካከል ጠንካሮች ናቸው ብለው ያሰቧቸውን እየመረጡ በመግደል ሥራ እንዲሠማራ ማድረግ ነው፡፡

የብአዴን ተልዕኮም እነፕሮፌሰር አሥራትን በመግደልና በማሥገደል እንዲሁም ትነግ(ኢሕአዴግ) በኦሮሞ(ብልፅግና) ሲተካ የሚቆም ሳይሆን፣ <u>”ሥርዓቱ፣ህገመንግሥቱና የዘር ፌደራሊዝሙ”</u> እሥከቀጠለ ድረስ ቆመን ካልመከትን የአማራው ሠቆቃ ይቀጥላል።እሥካሁን እየሆነ ያለውም ይኸው ነው።

ፀረአማራው ትነግ(ኢህአዴግ) አሥራትን የጥቃት ሠለባ ለማድረግ የሀሰት ክሶችን ደርድሮ ካሠረ በኋላ፣ ከእሥር ቤት ወደፍርድ ቤት፣ከፍርድ ቤት ወደእሥር ቤት ሲመላለሱ ለእንግልት እና ለተጨማሪ በርካታ በሽታዎች ተዳረጉ።ይሄ ቢታወቅም በጊዜው አሥፈላጊውን ህክምና በመነፈጋቸው በበሽታው ሲሰቃዩ ከቆዩ በኋላ፣ለይስሙላ ህክምና ይሰጣቸዋል እየተባለ በሀኪም ቤት ምልልስ ብቻ ከፍተኛ መጉላላትና የሞራል ጥቃት እንዲደርስባቸው ተደረገ፡፡ በዚህ ጊዜ በሽታው ቀስ በቀስ እየጎዳቸው እንዲሄድ ሆን ተብሎ ሥለተሠራበት ሥር እየሰደደ ሄዶ አሥጊ ደረጃ ላይ ሲደርስ ሆስፒታል ገብተው ተስፋ በሌለው ሕክምና ቆይተው፣ነገ ዛሬ ህይወታቸው ያልፋል በሚል ሥጋት ላይ እንዳለን፣ለተሻለ ህክምና ወደውጭ አገር ሄዱ፡፡ ቢሄዱም አሁንም ተስፋ በማይሰጥ ሕክምና ቆይተው አረፉ።

ዘረኞቹ ትግሬዎችፕሮፌሰር አሥራትን በማምጠጫ ዕድሜያቸው ወቅት በፈጠራ ወንጀል አሥረው አምስት ዓመት አንገላተውና አሠቃይተው በቁመና ከገደሏቸውና እንደማይድኑ ካረጋገጡ በኋላ፣ለይስሙላ

ህክምና ወደውጭ አገር ማስወጣታቸው በዘረኞቹ ላይ የሚመጣውን የሕዝብንና የዓለምን ተቃውሞ ለማርገብ እና ሠብዓዊ መሥሎ በመቅረብ የፖለቲካ ትርፍ የሚያሥገኝላቸው ሳይመሥላቸ አልቀረም፡፡ ይህ ድርጊት የሚያሳዬው ዘረኞቹ፣በአማራው ሕዝብ ላይ ያላቸውን መረን የለቀቀ ጥላቻና ፋሽስታዊ ተልዕኮ በመሆኑ፣ቁጣችን አይሎ፣ጥርስ እንድንነክስ ለመሆን በቅተናል።

ዘረኞችንና ባንዳዎችን በልበሙሉነትና በጀግንነት ሲታገሉ፣በማይቀረው የሠው ልጅ መጨረሻ በሆነው ሞት በአካል ከእኛ የተለዩን ፕሮፌሰር አሥራት!ጉልበታቸውን፣ዕውቀታቸውን፣ገንዘባቸውንና ዕምነታቸውን፣ ብሎም ህይወታቸውን አሳልፈው የሰጡት፣በቅድሚያ የአማራው ዘር ከምድረገፅ እንዳይጠፋ በመከላከል ህልውናውን ተግባራዊ ለማድረግ፣ቀጥሎም ለአገርና ለሕዝብ አንድነትና ነፃነት ሲሉ ነበር።

ጀግኖች ግብና ዓላማ ቀርፀው የሚራመዱ በመሆናቸው ድፍረት፣ልበሙሉነትና አይበገሬነት መለያቸው ሥለሆነ፣ታላቅነት ከውስጣዊ ጀግንነት ሥሜታቸው ሥለሚመነጭ ምንጊዜም ከትግሉ ግንባር በቅድሚያ የሚቆሙ የትግል ፋና ወጊዎችና ገድል ፈፃሚዎች ናቸው።መከራና ፈተና አይበግራቸውም።ድሎት አያታልላቸውም።ለህዝብ ኖረው፣ሥለሕዝብ ታግለው፥ለሕዝብ ሲሉ ሕይወታቸውን ሠጥተው ያልፋሉ።

በየዘመናቱ ያለፉ የሀይማኖት አባቶችንም ሆነ የአገር መሪዎችን ፣ለምሳሌ የእነአፄ ቴዎድሮስን ተጋድሎ ሥናጤን፣"ለጠላት እጄን አልሰጥም" ብለው፣የጠላትን ቅሥም ሰብረው ለወገናቸው የጀግንነት ገድል አሥመዝግበው ማለፋቸውን እናስታውሳለን።ፕሮፌሰር አሥራት! የእነዚህ ትውልዶች አደራ ተረካቢ፣ የዘመናችን ታላቅ ሠው፣የፅናትና የልበሙሉነት፣የሀቀኝነትና የብልህነት፣የአርቆ አስተዋይነትና ሚዛናዊነት ተምሳሌት በመሆን፣ለህይወታቸው ሳይሳሱ ጠላትን ፊት ለፊት ተጋፍጠው ያለፉና በእያንዳንዱ ወገናቸው ልብ በህያውነት የሚታወሱ ናቸው።

ዛሬ ፕሮፌሰር አሥራት ቢያልፉም፣ዓርማውን አንግበው፣በአይበገሬነት ሞትን እየሞቱ ለመታገል የቆረጡ እንደ እንጉዳይ የፈሉና እሳት የላሱ ሚሊዮን ወጣት አሥራቶች መፈጠራቸው እሠዬው የሚያሠኝ ነው፡፡

ለዚህም ሩቅ ሳንሄድ በቅርቡ የአቢይ አህመድ ኦሮሞዎች በአጣዬ የአማራን ዘር ከእነከተማው ሲያጠፉ፣ የአማራው ወጣት ቀፎው እንደተነካ ንብ በመትመም "አትግደሉን! በቃን! ይህ የመጨረሻ ሠልፋችን ነው!ከእንግዲህ ሠልፍ አንወጣም!" ብሎ ብሶቱንና ምሬቱን፣ፍፁም ሠላማዊ በሆነ የሠልፍ ማዕበል መግለፁ ተጠቃሽ ነው፡፡

ይህንን ሠላማዊ ሰልፍ አሥመልክቶ አቢይ በአማራ ሕዝብ ላይ ያለውን ንቀት "ጫጫታ" በሚል ገልፆታል።ብአዴንም ከሠልፉ በኋላ እያሠረ ይገኛል።

አማራው!ለራሱ ደህንነት የሚቆምለት መንግሥትም፣መከላከያም፣ ፌዴራልም እንደሌለው እና ጠላቱን በሚገባ አውቆ ግልፅ ያለ አቋም ይዞ እራሱን አደራጅቶ ማንነቱን ለማሥጠበቅ እና ኢትዮጵያን ከዓለም ካርታ አጥፍተው በኦሮሚያ አገር ሊተኳት የሚንደረደሩትን ለማሥቆም፣ መሣሪያውን ታጥቆ እሥካልተነሳ ድረስ በምናብ ብቻ "አለች" እያለ ራሱን ቢያታልል ሠቆቃውን አራዝሞ ከእነኢትዮጵያው ጭምር ከምድረ ገፅ መጥፋት ነው ያለው ዕድል።

ሥለዚህ ጠላቶቻችን በመታጠቃቸው እኛን እንደከብት እንደሚነዱንና ሳያጠፉንም እንደማይተኙ ተረድተን ፣መፍትሄው ቱትሲዎች ዘራቸውን ለመታደግ የሄዱበትን መንገድ መተግበር ብቻ መሆኑን ማመን የግድና ጊዜ የማይሠጥ ነው።
የህቡዕም ይሁን የሽምቅ ት.ትግል! የፖለቲካ ንቃት ባላቸው አማራዎች የሚመራ ከብአዴን ተፅዕኖ ውጭ ልዩ ኃይሉን፣ፋኖውንና ሚሊሺያውን ያካተተ ለአማራው ሕዝብ የደህንነት ዋሥትና የሚሆን የህቡዕ ት.ትግል ግን ወሳኝ ነው።

ይህ ሲባል ግን በሠላም ትግል የቆመው "አብን" የሚያደርገውን ሠላማዊ ትግል ለማሳነስ አይደለም።አብን! እሳት ውስጥ ሆኖ የሚሄድበት የመዐሕድ ዓይነት የሰላም አካሄድ አምባገነን ገዥዎች "ዴሞክራሲ አለ ወዘተ"የሚሉበትን ሜዳ ተጠቅሞ ማጋለጥና አማራውን በተገኘችው ቀዳዳ ተጠቅሞ ለማንቃት ጥረት ማድረጉ የሚያሥመሰግነው ነው።ድጋፍም እንሠጠዋለን።ይህን ከማድረግ ውጭ ሌላ ነገር እንዲያደርግ አማራው መጠበቅ የለበትም፣ምክንያቱም የቆመው በሥላማዊ ትግል ብቻ ሥለሆነ፡፡

ከዚህ ቀጥዬ በሌላው በፕሮፌሰር ትምህርት ሠጭ ንግግር ልቋጨው፡፡

“ዛሬ ታላቁ የዐማራው ጠላት ዐማራው ነው።አንዳንድ የደላውና ዐወቅሁ ባዩ፣የዐማራ ድርጅት በመቋቋሙ አልሥማማም እያለ ሲዋልል፣ሌላው ደግሞ በጠቋሚነት፣በአሳባቂነት፣በአድርባይነት፣በገዳይነት የገዛ ወንድሙን ለዕለት ሆዱ ፍላጎት ሲል ከፍተኛ በደል እያደረሰ ነው።እሥካሁን ድረስ የተሠራው ተሠርቷል። ከእንግዲህ ወዲህ ግን እንደነኒህ ያሉትን፣ጠላትነታቸውን እንዲያውቁ ማድረግና ይሉኝታም ስፍራ የሌለው መሆኑን በጥብቅ ልናሳስብ እንወዳለን።በሌላ በኩል ሌላው የዐማራ ክፍል ተኮላሽቶ፣ተኙቶ በማንቀላፋት ላይ ይገኛል።ይህ ክፍል ቢቃጠልም እንኳ ሊሠማው ስላልቻለና አልነቃም ብሎ ስለቀረ፣ያለው ዕድል እንደሚባለው"ዐማራው ሲተኛ የሚበላው ጅብ ነው።"" ይህንን ነበር ያሉት ።ይህ ችግር ዛሬም ተንሠራፍቶ ይገኛል።ፕሮፌሰር ያሉትን ሰምተን ተግባራዊ ለማድረግ ቆርጠን ተነሥተን ቢሆን ኖሮ ይህ ዛሬ ያለው ችግር በተቀረፈ ነበር።ዛሬም አልመሸም።

ይህ በዚህ እንዳለ!የአሥራትን ውለታ እንዴት እንከፍላለን ሥንል፣ የትግል ዓርማቸውንና የመንፈስ ጥንካሯቸውን ተላብሰን በመታገል ነው።በኢትዮጵያ ምድር የዓሥራት ዓላማ ተግባራዊ እሥከሚሆን ድረስ ትውልድ ሁሉ ትግሉን መቀጠሉ ውለታ ከፋይነቱን የሚያረጋግጥ ይሆናል።

በመጨረሻ! ለአማራው ህልውናና አንድነት ቀናኢ የሆነው ሁሉ፣ፕሮፌሰር አሥራት!ታሪክና ትውልድ የማይረሳው ተግባር ፈፅመው በማይቀረው የሠው ልጅ መጨረሻ በሆነው ሞት፣ከዚህ ዓለም የተለዩበትን 22ኛ ዓመት አሥመልክቶ በታላቅ ሀዘንና ቁጭት አሥቦት እንዲውል እያስታወስን፣ይህን ዕለት ከሕዝባችን ተስፋና ድል ጋር አያይዞ የሚከበርበት ወቅት አሁን ባለው የጊዜና የሁኔታ ውስብስብነት ቢዘገይም አይቀሬ መሆኑን ሳናሰምርበት አናልፍም።

የሰማዕቱ የአሥራት ሥራ ህያው ሆኖ ለዘለዓለም ይኖራል!

ለአማራው ህልውናና ለነፃነት የሚደረገው ትግል እሥከድል ይቀጥላል!

ሞት ለፀረ-አማራዎች

አያሌው ፈንቴ